# 26ኛው የግንቦት 20 በዓል ፓሪስ በሚገኘው የኢፌድሪ ኢምባሲ በድምቀት ተከበረ

26ኛው የግንቦት 20 በዓል ፓሪስ በሚገኘው የኢፌድሪ ኢምባሲ በከተማውና በአከባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት እ.ኤ.አ ጁን 3 ቀን 2017 በታላቅ ድምቀት ተከበረ፡፡ በዓሉ በፓለል ወይይት የተከበረ ሲሆን፣ በፈረንሳይ የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር የሆኑት ክቡር አምባሳደር ነጋ ጸጋዬ የፈረንሳይ የአውሮፓና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር Mr Jean-Yves Le Drian ለኤምባሲውና በፈረንሳይ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለግንቦት 20 በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን ለተሳታፊዎች በመግለፅ የፓነል ውይይቱን ጀምረዋል፡፡ በመቀጠልም ክቡር አምባሳደር ነጋ የኢፌዲሪ ህገመንግስትና የፌዴራል ስረዓታችን ልዩ ባህሪያት፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ ባለፉት 26 ዓመታት የተገኙ ወጤቶች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ትኩረት አድርገው በስፋትና በጥልቀት ከ300 በላይ ለሚሆኑ የበዓሉ ታዳሚዎች አቅርበዋል፡፡




በተጨማሪም ክቡር አምባሳደር ነጋ ባቀረቡት የመወያያ ነጥብ ገዥው ፓርቲና መንግስት እያደረጉ ያሉት ጥልቅ ታሃድሶ ሂደትን በስፋት በማብራራት ይህ ጥረት ግቡን በሚፈለገው ደረጃ ሊመታ የሚችለው የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲታከልበት መሆኑን አስገንዝበው፣ ዳያስፖራው በዚህ ሂደት ንቁ ተሳትፎ እንድያደርግና ገንቢ ሚና እንዲጫወት ጥሪ አቅርበዋል፡፡ በመጨረሻም ከተሳታፊዎች በተነሱት ጥያቄና አስተያየቶች እንዲሁም በተነሱት ጥያቄዎች ላይ በተሰጡት ማብራሪያዎች ውይይቱን በማዳርር በመግባባት ተጠናቋል፡፡





በበዓሉ አከባበር ለይ የተገኙ የዳያስፖራ አባላት ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖ የአለም ጤና ድርጅት ዳይረክተር ሆነው በመመረጣቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል፡፡ በዚሁ የግንቦት 20 በዓል አከባበር ስነስረዓት ላይ ከዚህ በፊት 6ኛው የኢተዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረተ-ድንጋይ የተጣለበት በዓል በኢምባሲው ሲከበር ቦንድ ለመግዛት

ቃል የገቡና በዕለቱ ቃላቸውን ጠብቀው ቦንድ ለገዙ የዳያስፖራ አባላት ክቡር አምባሳደሩ የቦንድ ሰርቲፍኬት ሰጥተዋል፡፡




